ዴሞክራሲያ
* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 44 ቁ. 1 መስከረም 2011

# የአርባ አራት ዓመት አኩሪ ትግል

የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ከ2010 ዘመነ ማርቆስ፤ ወደ 2011 ዘመነ ሉቃስ በመሸጋገር አዲሱን ዓመት፤ በባሕሉ መሠረት፤ በሚችለው አቅሙ በማክበር፤ የህይወት ጉዞዉን ጀምሯል። ይጣፍጥም ይምረርም፤ ካለፉት ጊዜያት በተለየ ሁኔታ አዲስ ተስፋውን ሰንቆ ቀጥሏል። እንደበፊቱ ሁሉ አሁንም፣ ሁሉም ዜጋ ለተለያዩ እንግልቶች የዳረጉት ችግሮች እንዲወገዱለት ይመኛል። ፀጋውና በረከቱም እንዲበራከቱለት ይጓጓል። አዲሱ ዓመት የደስታና የሰላም ዘመን እንዲሆንለት ይፈልጋል። የመኖሪያ ቤቱን ሆነ ጎጆውን በቁጠማና በፀደይ አበባ አድምቆ - ደግሶ ከወዳጅ ዘመዶቹ ጋር አብሮ ለማክበር፤ የሚያስችለውን ሠላምና መረጋጋት ሰፍኖ ማየትን ቢመኝም፤ ምኞቱ ግን እንዳሰበው አልሆነለትም። አሁንም ሞትና ግድያ፤ መፈናቀል፤ ዋይታና ጩኸት፤ በኢትዮጵያ ሀገራችን ሰማያት ላይ ያንዥብባሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቸውም ጊዜ በከፋ መልኩ፤ ዛሬ የተረጋጋ ሕይወት ናፋቂ ሆኗል። ሠላምን ቢመኝም ፤ ሠላምን ግን አላገኘም። የሚመኘውን ሠላም ለማግኘት ደግሞ ፤ በራሱ ምንጭነት የቆመ፤ ሕዝባዊ-ዴሞክራሲያዊ-ኢትዮጵያዊ መንግሥት ያስፈልገዋል። ያ ካልመጣ፤ የዘመን መለዋወጥ ብቻውን ትርጉም የለሽ ነው።

የዘንድሮውን የአዲስ ዓመት አቀባበል ልዩ ያደረገው ደግሞ በበርካታ ዜጎቻችን መስዋዕትነት የተገኘውን ሁኔታ በመጠቀም የፖለቲካ ሥልጣኑን ለመጨበጥ የቻሉት ቡድኖች ፤ በመደመር ቃል ላይ የተመሰረተና በጣዕመ ቅላፄ የተሸበበ አነጋገርን ተንተርሶ፤ "ሠላም፤ ፍቅር፤ ኢትዮጵያዊነት፤ አንድነት..." እና መሰል ዲስኩሮች እየተሰነዘሩ መሰማታቸው ነው። አሁን የተከሰተው ሁኔታ ከተፈጠረ ጀምሮ አንዳንድ መሰረታዊ ያልሆኑ ለውጦች፤ ውስጣቸው ሲፈተሽ ግን ያንኑ የቆዩ ያሰራር ልምድ የተላበሱ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አጓጉዊ የተስፋ ጭላንጭል እንዳሳደሩ ታይቷል።

በርግጥም ቀድሞዉንም መታሰር ያልነበረባቸው በአገዛዙ ፖሊሲ ላይ ተቃውሞ በማሰማታቸው ብቻና በተለያዩ የጥፋት ወንጀሎች (ሽብርተኛ "ቴረሪስት" በሚል ጭምር) ተፈርጀው ወህኒ እንዲወርዱ የተደረጉ ብሎም፤ ለተለያየ ስቃይና እንግልት ከተዳረጉት ዜጎች መካከል፤ የተወሰኑቱ ተፈትተው ከቅርብ ዘመዶቻቸው መገናኘት፤ እንደዚሁም፤ በእምነት ተቋማት ውስጥ የተከሰቱ ልዩነቶችን ለጊዜውም ቢሆን ረገብ እንዲሉ መደረጋቸው፤ በተወሰነ ደረጃም በሻዕቢያ ከምትመራው ኤርትራ ጋር " የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት" መጀመር፤ በተለያዩ ከተሞች ከጅግጅጋ አንስቶ ሃዋሳ፣ መቀሌ፣ ...ወዘተ የጥያቄና መልስ ስብሰባ መደረግ፤ በባዕዳን ሀገርም አሜሪካ አንዳንድ ከተሞች ተመሳሳይ እንቅስቃሴዎች መደረጋቸው፤ በሽብር ወንጀል ክስ ከተመሰረተባቸው ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች መካከል ጥቂቶቹ፤ ከሚገኙበት የባዕድ ሀገር ወደ ሀገራቸው ለመግባት መቻል፤ እንደ "የለውጥ እርሾ ተደርገው" በመወሰዳቸው፤ የተወሰነውን ህብረተሰብ ክፍል ማማለላቸው የማይጠበቅ አልነበረም ።

ይህ ሁናቴ ግን እምብዛም ወደፊት እንዳላስኬደ በሚያስደነግጥ ፍጥነት በተለያዩ አካባቢዎች በተደረጉ አሰቃቂና አሳዛኝ ድርጊቶች ሊታይ በቅቷል። ለዚህ ምክንያቱ ልዩ ሚስጢር ኖሮት ሳይሆን ፤ ባለፉት 27 ዓመታት እንደ ያንድ ሀገር ህዝብ አንድ ከሚያደርጉን እሴቶችና ዜጋዊ ትስስር ይልቅ በልዩነቶች ላይ ያቀነቀነ መርዝ በመላው ሀገሪቱ በመነዛቱ ነው። ሕዝቡ፣ በየጊዜው በሚቀሰቀሱ ግጭቶች አማካይነት እንግልት፣ ሞትና ከቀዬው መፈናቀል፣ መሰደድ እየደረሰበት አሁንም ድረስ መፍትሄ ለመስጠት ባለመቻሉ ነው። በቅርቡ በቡራዩ ከተማና አካባቢው የተከናወነውን ግድያና የህዝብ በገፍ መፈናቀል በሚያሳዝንና ልብን በሚያቆስል ስሜት ታዝበናል። ይህን የዜጎችን ስቃይ ለመታዘብ የተገደድነው፤ ቀደም ሲል ከነበሩት ተመሳሳይ ድርጊቶች ጋር ተዳምሮ፤ ሀገራችን የወደቀችበትን አደጋ አመላካች መሆኑን በማሰብ ነው። ባለፉት ዓመታት

ሀገራችን ውስጥ እየታየ ያለው መጠነ ሰፊ ግድያና መፈናቀል ልዩ የሚያደርገው ነገር ቢኖር፣ ፍትህ እንዳይገኝ የዜጎችን ሕይወት በከንቱ ያጠፉ፣ ለልዩ ልዩ ሰቆቃ የዳረጉ፤ የሕዝብ ንብረት የዘረፉ፣ ሕዝብን ከቀዬ ያፈናቀሉ፣ አገር ያስደፈሩና ድንበር በማፍረስ መሬት በመቁረስና ነዋሪውንም አፈናቅለው የሸጡ ሁሉ አሁንም በአገዛዙ ሥልጣን ላይ ይገኛሉ።

ልዩ ልዩ ወንጀል የፈጸሙ ሁሉ፤ ይቅርታን ሳያገኙ፤ ከኃጢያታቸው ሳይፀዱ፤ ከበደሉት ዜጋ ጋር፤ በበደሉት ሕዝብ መካከል በሰላም እንዲኖሩ መደረጋቸውና በወሳኝ የሥልጣን ቦታ አሁንም ድረስ እንዲቆዩ በመደረጋቸው የሠላም እንቅፋት ሆነዋል። ለሚካሄደው ለውጥም እጅግ ሲበዛ፤ የአደጋ ምንጮች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ፤ የሕዝብ ትግል በዋናው ጠላት ላይ እንዳያተኩር እንቅፋቶች ሆነዋል። "ሰላም፥ ፍቅር፥ ኢትዮጵያዊነትና አንድነት" የተሰኙ አነሁላይ ቃላት፤ ሕዝባዊው ትግል አቅጣጫውን እንዲስት እያደረጉት ይገኛሉ። ጉራ ፈርዳ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያና ሶማሌ አካባቢዎች ፣ እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች ቁጥሩ ይለያይ እንጂ ዜጎች የዚህ መርገምት ሰለባ የሆኑባቸው ሥፍራዎች መሆናቸው ምንጊዜም ሊረሱን የማይገቡ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ሆነውብናል።

ባለፈው ግማሽ ምዕተ ዓመት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የደረሱት ጥፋቶች፤ በኢትዮጵያዊያን የተፈጸሙ በመሆናቸው የኛው ታሪክ ናቸውና መፍትሄ ፈላጊዎቹም ከኛ ሌላ ማንም ሊሆን አይችልም የሚል የፀና ዕምነት አለን። ይህም ያለምክንያት አይደለም። በተደጋጋሚ ግልፅ ለማድረግ እንደተሞከረው የሕዝባችን ትግል በጫንቃው ላይ የተቆናጠጠውን አገዛዝ ከፉኛ ባስጨነቀበትና ድልን ሊቀዳጅ በተቃረበበት ወቅት፤ በባዕዳን ሴራ በትግላችን ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ሲቸለስበት ማየት አንጀት ያቆስላል። በ1982 ዓ.ም ደርግ ወድቆ ወያኔ ሥልጣን እንዲይዝ በለንደን የተደረገው ስብሰባና ውጤት መቼም የማንረሣው የባዕዳን አይን አውጣ ጣልቃ ገብነት በምሳሌነት የምንጠቅሰው መሪር ቁጭት ነው። ወያኔ በ27 አመት የአገዛዝ ዘመኑ ያደረሰውን ጉዳት መዘርዘር ለቀባሪው ማርዳት ስለሚሆንብን እናልፈዋለን። በአሁኑ ወቅትም የወያኔ አገዛዝ በሕዝብ ትግል ከታሪክ ትቢያ ለመጣል በተደረገው ሂደት የተደናገጡ ባዕዳኖች ዳግም የሴራ ተልዕኳቸውን፤ ለዳግመኛ ጣልቃገብነት የሚሰሩትን እየሰሩ ይገኛሉ። ኢትዮጵያ ሀገራችን ጥቅሟን የሚያስከብርላት ሁነኛ የዲሞክራሲ ሥርዓት አስተናጋጅ የፖለቲካ መሪ የሌላት መሆኗን ተረድተው፤ ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅላቸው ቡድን መኖሩን በማረጋገጥ ለይ ናቸው። ይህ ሴራ በመሳካቱም፤ በድል ሊጠናቀቁ የሚገባቸው የሕዝብ ትግሎች ለጊዜውም ቢሆን ተዳከሙ። በዚህ ብቻ አላቆመም። ኢትዮጵያዊ ኃይሎችንና ኢትዮጵያዊነትን የማዳከም ሥራ ይበልጥ እንዲቀጥል ተደረገ። ሕዝብ የማንነቱ መገለጫ የሆነውን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለም ያሸበረቀ ሰንደቅ ዓላማውን አክብሮና አውለብልቦ በመገኘት ብሔራዊ ስሜቱን ቢያስረግጥም፤ በተቃራኒው ኢትዮጵያዊነትን የማዳከሙ ተግባር ዋና አላማቸው የሆኑ የገንጣይና አስገንጣይ ቡድኖች የፖለቲካ መድረኩን ለመቆጣጠር ይቻላቸው ዘንዳ አዲስ አበባና የተለያዩ ትላልቅ ከተሞች ዋና ተዋናይ ለመሆን መቻላቸውን እንታዘባለን። የዚህ ሴራ ውጤት ደግሞ ዝርዝሩ ከግልፅም ግልፅ ሆኖ ተገኝቷል። ሴራ በዚያው ልክ ተፋፍሞ እነሆ ዛሬ የግንጠላ ኃይላት ሁሉ መድረክ ያገኙበት፤ ሰንደቅ ዓላማ የሚዋረድበት፤ የግንጠላ አርማዎች የሚውለበለቡበት፤ ክርስቲያንና ቤተ ክርስቲያናት የሚቃጠሉበት፤ አማራ ጠላት ተብሎ የሚገደልበትና ፀረ አማራ ሀውልቶችን ለማቆም መሠረት የሚጣልበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል።

ለዚህም ነው ለትግሉ አቅጣጫ ሊሰጡ የሚገባቸው የፖለቲካ ኃይሎችንና ታዋቂ አገር-ወዳድ ግለሰቦችን፤ ለማታለልና ለማጃጃል በመሞከር፤ ይህ ሁናቴ ቀጣይነት እንዲኖረው ለአዲሶቹ ባለሥልጣናት መመቻቸት እንደሆነ ልሂቃን የቆጠሩት። አስመሳይና አሳሳች የሀገር ወዳድነትን ካባ ለመላበስ ለሚጥሩ ሁሉ፤ ሙከራቸው፤ የኢትዮጵያዊያን ባህል እንዳልሆነ ሊሆንም እንደማይችል ሊረዱት ይገባል። አዲሱ ሹመኛ ደግሞ ከሥልጣን ከተቆናጠጠ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ሰላም፥ ፍቅር፥ ኢትዮጵያዊነትና አንድነት የሚለውን የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳውን ከመስበክ የሚያልፍ አልሆነም። ለተከሰቱት አሰቃቂ ችግሮቻችን መነሻ የሆነውና የወያኔ ሕገ-መንግሥት ተብየውን ዝባዝንኪ ሠነድ ምንም ሳይመክርበት የተጫነበት በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኔ አይደለም እያለ ነው። በ1983 ዓ.ም ተግባራዊ እንዲሆን የተወሰነውን የእርኩስ ተግባር ማስፈፀሚያ ተብሎ የተሰየመ በመፅሃፍ መልክ የተጠረዘውን የወያኔን የፖለቲካ ፕሮግራም ሠነድ፤ እንደ ሳጥናዔል እርኩስ መጽሐፍ ተሳልሞ ተግባራዊ አደርጋለሁ በማለት ቃለ መሃላ የፈፀመው፤ የሰነዱ ምርኩዝ ፤ የዘረኛ ድርጅት መሆኑን በሚገባ ሊመለከቱት አልፈቀዱም።

ይህ ሁናቴ የሚያስገነዝበው አንድ ቁም ነገር ቢኖር፤ በሁለቱ አቋሞች መካከል ሊታረቅ የማይችል ቅራኔ መኖሩንና ይህ ቅራኔ ደግሞ በሕዝቡ ፍላጎትና ትግል መፈታት እንደሚኖርበት ነው። እስካልተፈታ፤ ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገው የጥፋት ሰነድ ከዘር፣ ከቋንቋም ሆነ ክልሎች ጭምር እስካልተለወጠ ድረስ ፣ ትናትናም ሆነ ዛሬ የብዙሃኑን ሕይወት እያመሰቃቀሉ ያሉትና ፋታ ያሳጡት መጠነ ሰፊ የሆኑ ችግሮቹ ቀጣይነት ያላቸው መሆኑን ነው። በመሆኑም በበኩላችን፤ የገፈቱ ቀማሽ የሆነው ሰፊው ሕዝባችን የመፍትሄ ፈላጊም አመንጪም ራሱ መሆኑን በሚገባ ተገንዝቦ ወቅቱ የጣለበት የራሱን ኃላፊነትና

ግዴታውን ለመወጣት ፤ ከግለሰብና ከድርጅት በላይ እያሰበ፤ ዘላቂ መፍትሄ ሊያስገኝለት ወደሚችለው የትግል አቅጣጫ ማትኮር ይገባዋል ብለን እናምናለን።

ተደጋግሞ ለመግለፅ እንደተሞከረው የለውጥ እርሾዎች ፍሬ የሚያስገኙት ፤ በመልካም ምኞቶችና በቀቢፀ-ተስፋ ሳይሆን፤ በሕዝባዊ ቆራጥ ትግል ብቻ መሆኑን ማመን ይገባል። የትግሉን ፍሬ እራሱ አምጪው ኃይል ተግባራዊነታቸውንም እያረጋገጠ ብቻ ሳይሆን፤ እንዳይነጠቅም አስፈላጊውን ጥበቃ ለማድረግ ካልቻለ ትርፉ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ነው። የነፃነት ቀኑንም ማርዘም ይሆናል። የጭቆና ቀንበርን መሸከም በቀጣይነት እንዲራዘም ማድረግና ራስንም ለከባድ ቀንበር መሸከም ማመቻቸት ጭምርም ይሆናል። የተወሰኑ ግለሰቦችን እንደ ሁሉን አድራጊና ፈጣሪ አድርጎ በመመልከት፤ መሰረታዊና ዘላቂ የሆነ ውጤት ሊገኝ እንደማይችል ከተመክሮ የተገነዘብነው ሐቅ ነው። በመሆኑም ይህ ዓይነቱ መጃጃል ሊታረም የሚችለው፤ ባለፉት ጊዜያት ስለደረሰብን ጥቃትም ሆነ ፍላጎታችን ያለመሳካቱ ሁኔታ ያሳደረብን ቁጭት፤ አዲሱን ዓመት ለችግሮቻችን መፍትሄ ፍለጋ አዳዲስ ዘዴዎችን እንድናመጣ የገፋፋናል። ይህንን የቁጭት ግፊት እውን የምናደርገው፤ መሠረታዊ ለውጥ ለማስገኘት የሚያስችለን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ቆርጠን የመነሳቱ ጉዳይ ግዴታችንና ኃላፊነታችንም ጭምር መሆኑን ስንገነዘብ ብቻ ነው። እልህ አስጨራሽ ከሆነ የፖለቲካ ትግል መሸሽ፤ እያንዳንዳችን ያለንን ለራሳችን የመወሰን ኃላፊነት በመሸሽ አይደለም። በመሻርና በመደመር ፖለቲካ ሥር ተኮልኩለን፤ ለችንፈት መዳረግ ሀገር ወዳድነትንና ለሕዝብ ፍቅር ቀናዒነትን ከቶ አያመላክትም። የታጋይነት ካባንም አያላብስም። ግላዊ ነፃነትን በገዛ ራስ መድፈቅ የሚሆነውም በዚሁ ምክንያት ነው። ይህንንም መፍቀድ ከበደልም በደል ነውና ጨርሶ የሚወገዝ ነው። አፈሩ ይቅለላቸውና መስዋዕቶቻችንንም ማርከስ ነው የሚሆነው። ውርደትን መከናነብ የኢትዮጵያውያን ባሕል መሆን እንደሌለበት አያት ቅድም አያቶቻችንም ሆነ በዚያ ትውልድ ስያሜ የሚጠሩት አባላቱ በገድላቸው ያረጋገጡልንን የታሪካችንን ቅርስ አለመጠበቅና ተገቢ ቦታውንም መንፈግ ነው። የዛ ትውልድ የበኩር ልጅ የሆነው ኢሕአፓ ከዚህ የተለየ ልዩ ዕምነት እንደሌለው የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎቹ መስካሪዎቹ ናቸው።

በተለያዩ አካባቢዎች የተደረጉት እንቅስቃሴዎች የሚያሳዩን ዕውነታዎች፤ አሁንም የአገራችን ሠላምና አንድነት አደጋ ውስጥ እንደሚገኙ ነው። ሥርዓት አልበኝነት ፤ ሕገ ወጥነት፤ የደቦ ፍርድ፤ ብሔርና ኃይማኖትን ያስታከከ ግጭት፤ የጸሎት ቤቶችን ማቃጠል፤ የኃይማኖት አባቶችን መግደል፤ ህፃናትንና እናቶችን መግደል፤ የሰውን ንብረት መዝረፍ ሁሉ የሚያመላክቱት፤ ይህንኑ አግጥጦ-አፍጥጦ የመጣ አደጋ ነው። አዲስ ሹመኛ ከመጣም ወዲህ የጎሳ ፖለቲካ በቀጣይነት ተግባራዊ ሆኖ ይገኛል። የዚሁ መሐንዲስ የሆኑት ባለሥልጣናትና ተላላኪዎቻቸው ተዳከሙ፤ ምሽጋቸውን ሌላ ቦታ አደረጉ እንጂ ጨርሶ አልተወገዱም። መደመር ተብሎ ነጋ ጠባ የሚደረገው መጠነ ሰፊ በአፈቀላጤ ተደማሪዎች የሚደረገው ሰበካ ቀድሞውኑ በኢሕአዴግ የተቀነቀነውን አዲሱ ባለሥልጣን ያሳመረለትን የጥገና ጎዳና ተከተሉ፣ ሕዝብንና አገርን ለመከፋፈል መሰረት የሆነውን የጥፋት ሰነድ አክብሩ፤ ተጎንበሱና ከእግሩ ተነጠፉ፤ ስገዱ-ተሳለሙ ከማለት ውጭ በሌላ አይተረጎምም።

ለአጼውም ሆነ ለኮሎኔሉ እምቢኝ አሻፈረኝ ላልነውና ለታገልነው ያን ሁሉ መሥዋዕት ለከፍልነውና አሁንም እየከፈልን ላለነው ሀገር ወዳድ ታጋዮች መቅረቡ በውነቱ ልናደርገው ቀርቶ ሊታሰብንም የማይችል ኩነት ነው- የጥገና ለውጥ። አጥብቀን የምንቃወመው፤ የምናወግዘውና በውስጡ ያዘለውንም የተንኮል ሴራ መጋለጥም ያለበት ነው እንላለን። ለዚህም ነው በበኩላችን እንደ ኢሕአፓ የጠየቅነው የሽግግር ሂደትና ማንንም ያላገለለ ሁሉን አቀፍ የሆነ ዴሞክራሲያዊ የሽግግር መንግሥት ምስረታንም ሆነ የታሰሩት አባሎቻችን የመፈታት ጉዳይ ወደጎን ስለተደረገ ተስፋ ቆርጠን የምንተወው አይደለም። ይልቁንም ትግላችንን በፅናት ለመቀጠል ውስጣዊ ግፊት ይሰጠናል እንጂ። በሀገራችን የወደፊት ዕጣ-ፋንታ ማወቅና የመወሰን ከፍተኛ ባለሥልጣን የሆነው ሕዝባችን እንጂ ግለሰቦች ወይንም የተወሰኑ ቡድኖች ሊሆኑ ከቶም አይችሉም የሚል ፅኑ እምነት ያለን በመሆናችን ደጋግመን የምንጠይቀው።

በጥቂት ግለሰቦች ብቸኛ ተዋናይነት የሚደረጉትን ማናቸውንም ጥሩም ሆነ መጥፎ ተግባራት በቸልታ ማለፍ አንችልም። ማንንም ያላገለለ፤ ነገር ግን ሁሉንም ያካተተ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ፤ ለዘላቂ መፍትሄ መሠረት ነው ብሎ ያመነበተን አቋሙን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከማስረዳትና ያለመታከት ከመናገር ወደ ኋላ የሚልበት አንዳችም ምክንያት ስለሌለው ትግሉን ይቀጥልበታል። በተለይም የሚቀጥለውን ምርጫ ተብዬ ተውኔት በተለመደው ሁናቴ በአቸናፊነት ለመወጣት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን ከወዲሁ ማጋለጥ ሊያልፉት የማይችሉት ክስተት ነውና ከወዲሁ አጥብቀን የምንቃወመው በዚሁ ምክንያት ነው። ለዚህም ነው በማወቅም ሆነ በመጃጃል የነእንደመር ሰባኪዎች የሕዝብ ፍላጎት የሆነውን የሽግግር መንግሥት ጉዳይ ወደ ጎን ማድረግ ከአምባገነናዊነት ያልተለየ መሆኑን እንዲገነዘቡና ተደማሪዎች ከሴራው ተካፋይ ከመሆን ድርጊት ተቆጥበው የሕዝቡን ጎራ እንዲቀላቀሉ ጥሪ የምናቀርብላቸው። መደመር መብት ቢሆንም የሕዝብን ጥያቄ ወደጎን ማድረግ ደግሞ ፈፅሞ አግባብነት፤ ተቀባይነትም የሌለው በእጅጉም የሚወገዝ መሆኑን ሊያውቁት

የሚገባ መሆኑን አጥብቀን የምናሳስበው። ወደ ከርሰ መቃብሩ የተጠጋን ዘረኛና አምባገነናዊ ሥርዓት እድሜ ለመቀጠል በሚያስችለው ሂደት ከመሳተፍ መቆጠብ ብልህነትና የሚያስከበርም ነው።

ሁሌም ለመግለጽ እንደሞከረነው ሠላም የሙብት መከበርና የፍትህ መንገስ ውጤት ነው። ሠላም ማለት የጠብመንጃ ጩኸት አለመስማት፤ ምስማር አናቱ ላይ የተተከለ ጭንቅላት መደብደቢያ ዱላም ሆነ ሜንጫ አለማየት ሳይሆን፤ ለዘለቄታዊ ነፃነት፤ ለዘለቄታዊ ሰላም በሕዝብ ዘንድ እንደ ዐይን ብሌን እንክብካቤ ሊደረግለት ይገባዋል ማለታችን እንጂ፤ የምንፈልጋቸው ቃላትና አረፍተ ነገሮች ስለተዥጎደጎዱ ብቻና ለጊዜው እፎይታ ሰጪ የሚመስለንን መቀበል ሊሆን አይገባም። ከፍትህ ጋር ያልተዛመደ ሁናቴ ደግሞ፤ ሰብዓዊና ማህበራዊ ሠላምን ከቶም አያጎናፅፍም። እ.አ.አ በ1981 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መስከረም 21 ቀን ዐለም አቀፍ የሠላም ቀን ተብሎ እንዲከበር ሲወስን እንደገለፀው " ሠላም ማለት፤ የዜጎችን ፖለቲካዊ መብቶችን እንዲሁም ኤኮኖሚያዊ ዋስትናን፤ ሰብዓዊ ክቡርነትን የተላበሰ ኑሮ ለመኖር የሚያስችል ሁናቴን መገንባት ማለት ነው" ሲል ገልፖታል። ይህ ብቻ አይደለም። ሠላምና ማህበራዊ እድገት የተያያዙ እንደሆኑም አስቀምጧል። የማንኛውም መንግሥት ዋና ተግባሩ ለሕዝብ ህልውናና ሠላም ቅድሚያና ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ለአንድነቱ መጠናከርና መደርጀት፤ ለማህበራዊ እድገቱ፤ ለዳር ድንበሩ መጠበቅ ሌት ተቀን ቀና ጥረት ማድረግ ነው። በሀገራችን ይህ ሁናቴ ምንጊዜም ቢሆን ተሟልቶ ባለመገኘቱ ነው ካለፉት አምሳ ዓመታት ጀምሮ ይኸው እስካሁን ድረስ ሁለት ትውልድን ያሳተፈ፤ ከፍተኛ መሥዋዕትንም እየጠየቀ ያለ፤ ባንዱ ወይም በሌላ መልኩ  ሕዝባዊ ትግል እየተካሄደ የሚቀጥለው። በዚህም ምክንያት ነው "እንኳን በሠላም ከዘመን ዘመን አሸጋገረን " የሚለው አረፍተ ነገር ያለንበትንና የደረስንበትን ሁናቴ በአግባቡ የሚገልፅ ሆኖ የማናገኘው - አንድ ዜጋ በየትም ቦታ አላግባብ ሕይወቱ እየተቀጠፈ፤ አካሉ እየጎደለ፤ ከቤቱ እየተፈናቀለ ሌላው እኔ አልደረሰብኝም፤ በሰላም እየተሸጋገርኩ ነው ማለቱ አግባብነት የለውምና! ነፃነትን ተጎናፅፈን፤ የዜጎቻችን ምኞት ተፈፅሞ ቢሆን፤ የሀገራችን ሉዓላዊነት ተረጋግጦ ቢሆን፤ የሀገራችን ዳር ድንበር ተጠብቆ ቢሆን የዜጎቻችን አንድነትና እኩልነት ተረጋግጦ ቢገኝ፤ ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችን ተከብረው ከፍትህ ጋር የተዛመደ ዕውነተኛ ሠላም ነግሶ ቢሆን ኖሮ ከሁሉም በበለጠ ደስተኞች በሆንን ነበር። የአዲሱ ዓመት መምጣትም ሆነ  በዓላችንም እጥፍ ድርብ በሆነ ነበር። ግና ለዚህ ስላልታደልን ነው አዲሱን ዓመት በቀጣይ ትግል እናጅበው ማለታችን አግባብ ያለው የሚሆነው።

በመሆኑም፤ በነፃነት መርህ ላይ የተገነባ  "ሠላማዊነትን የተላበሰ የዘመን ሽግግር " ፤ በርግጥም ምኞታችን ከሁናቴው ጋር የተዛመደ ይሆን ዘንድ በቅድሚያ ካለፉት 28 አመታት ጀምሮ እስካሁን ድረስ በጫንቃችን ላይ ለመሸከም የተገደድነውን የወያኔን የዘረኝነት የአገዛዝ ሥርዓት ከጫንቃችን ማውረድ አስፈላጊ ነው። ሕዛባችን በነቂስ አንድነቱን ጠብቆ የኢትዮጵያዊነትን ዐርማና ማንነት ገላጭ የሆነውን ሰንደቅ ዓላማውን ከፍ አድርጎ በማውለውብለብ የነፃነት ድሉን እስከሚቀዳጅ ድረስ በፅናት መታገል ያለበት መሆኑን ፤ የ2011 ዓመት መልካም ምኞት መልዕክት እናስተላልፋለን። ባለፉት ጊዜያት እንዳስተላለፍነው ሁሉ ዘንድሮም የምናደርገው፤  የነቃ-የበቃ ፖለቲካ  በሁሉም የትግል ዘርፍ  ማካሄድ ወሳኝ ነው ብለን እናምናለን። ያልተደራጀውን ማደራጀት የተደራጀውን ደግሞ ማስተባበር፤ የተባበሩትን ደግሞ ሕዝባዊ አቅጣጫ በመስጠት ሕዝብ ለድል እንዲበቃ ጥረት ማድረግ ነው። ይህ ነው የ2011 ዓመት የመልካም ምኞት መልዕክታችን ሊሆን የሚገባው።

የወቅቱን ፖለቲካ ፤ በሕዝባዊ መነፅር ለሚመለከት ፤ በርግጥም ሊታይ የሚችለው በተለያዩ አካባቢዎች ከፍተኛ መሥዋዕት በመክፈል ለመሠረታዊ ለውጥ የተደረጉትና አሁንም እየተደረጉ ያሉት ትግሎች ስኬታማ እንዳይሆኑ በጥገና ለውጥ ለማኮላሸት የሚደረግ እንደሆነ ለመገንዘብ አያዳግትም። የሕግ የበላይነትና ፍትህ በነሱ እየተረገጠ እያለ ሕዝብ ሠላምና ሕግ አክባሪ እንዲሆን ይጠየቃል። የሚያደርጋቸው ተቃውሞዎች በሕገ ወጥነት ይተረጎምበታል። በሌለ የኤኮኖሚ ዕድገት ሊደልሉት ሲሹ አሻፈረኝ ማለቱ በሽብርነት ይወገዛል። የሕግ የበላይነትና ፍትሕ እየተረገጠ ባለበት ሠላም ተገኘ፤ ለውጥ መጣ ማለት የወንጀል ድርጊት ነው። ሲረገጥ እያዩ በመደመር ስም እያጨበጨቡ ለውጥ መጣ ማለት ጸረ ፍትሕ መሆን ማለት ነው። ከወንጀለኞች ጋር መደመር ማለት ፍትህን መርገጥ ብቻ ሳይሆን፤ የወንጀሉ ተባባሪን በተበዳይ ሰብዓዊነት ላይ እንዲያላግጥ ረግረግ ማመቻቸት ነው። በመሆኑም የመልካም ተግባር ዋና መሠረቱ ፤ የጭካኔና የአውሬነት ተግባርን በመጠየፍ የሕዝብ ወገንተኝነትን መለየት እንደሚገባ ሁሉ በዳይና ተበዳይንም በሚመለከትም የሥነ-ምግባር የበላይነትን ማረጋገጥ  በግድ ያስፈልጋል ማለት ነው።

ሕዝባችን የሞራል እውቀቱ ከፍተኛ ነው። ክፉና ደጉን በሚገባ የሚያውቅ በአማኝነቱም ቢሆን ለደግና ለመልካም ተግባራት በተለይም ደግሞ ለሰብዓዊ ክቡርነት ከፍተኛ ግምት ያለው በመሆኑ በመካከሉ ለሚከሰቱ ችግሮች በባህሉና በሚያከብራቸው እሴቶቹ ላይ በመመስረት ፍትህና ሠላም እንዲኖር የሚተጋ ነው። በሚያከብራቸው ዕሴቶቹ ላይ ለሚመሰረቱ ሕጎች ደግሞ ቀናኢነቱን በተደጋጋሚ ያስመሰከረ ለመሆኑ መንግሥት አልባ በሆነበት ወቅት ያደረጋቸው

ጨዋነትን የተላበሰ ሠላማዊነት ይመስክሩለታል። ሆኖም ግን ብዙ ሺህ ወገኖቻችን ውድ ህይወታቸውን የከፈሉበትና ገናም የሚከፍሉበት አገር- አድን ትግሉ ዳግም እንዳይነጠቅ መከላከል የሚቻለው፣ ሕዝባዊ ትግሉ በወያኔና ተመሳስለው በመሰለፍ፤ የተገንጣይ ዓላማቸውን ለማሳካት የሚያደቡ ቡድኖች ላይ ድልን ሲቀዳጅ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ የሕዝብን ይሁንታ ያገኘ፤ ሕዝብ የሥልጣን ምንጭ የሚሆንበት፤ የብዙሃኑ ድምፅ የሚገዛበትና የአናሳው መብት የሚጠበቅበት/የሚከበርበት፣ በሕግ ፊት እኩልነት፣ ነፃና ፍትሃዊ የሆነ የምርጫ ሕግ የሚከበርበት፤ ለመሠረታዊ መብቶች ዋስትና የሚሰጥበት፣ የመንግሥት ሥልጣን የሚወሰንበትና የሕዝብን ሉዓላዊነት ለጠበቀ (የህዝብ፣ በህዝብ፣ ለህዝብ ለሆነ) ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት የሚጥል የሽግግር መንግሥት ሲረከበው ብቻ ነው። ይህ የሽግግር መንግሥትም ስኬታማ ሊሆን የሚችለው ደግሞ በሕዝባዊ ትግል እንጂ በልመና እንደማይሆን እናውቃለን።

ሕብረተሰባችን በጋራ ድል ስኬታማ ሀገር ይፍጠር ከተባለ፤ ከዚህ የተሻለ ፍቱን መድኃኒት የለውም። ችግር ከተከሰተ በኋላ፤ ከጭፍጨፋ ከተረፉት ዜጎች ዘንድ ሄዶ፤ እምባ እያፈሰሱ፤ ልባዊ ሀዘኔታን ከመግለፅ በፊት፤ በሁሉም አካባቢ በተለይም ችግሮች ተከስተው በሚታዩበት ወቅትና ቦታ በፍጥነት ደርሶ ለማረጋጋት፤ ዘላቂ መፍትሄም ለመስጠት በጋራ ኃላፊነት ሁሉም ሊሰማው የሚችልበት ሀገራዊነትን ሲሸከም ብቻ ነው። ሁሉም እንደ ኢትዮጵያዊ ፈጥኖ ደራሽ ሊሆን የሚቻለው፤ ለከፉም ሆነ ለደጉ፤ ለመልካሙም ሆነ ለመጥፎው፤ ለደስታውም ሆነ ለሀዘኑ፤ ለእድገቱም ሆነ ለውድቀቱ፤ ለድሉም ሆነ ለሽንፈቱ፤ የጋራ ኃላፊነት ለመሸከም የሚቻለው ሁሉም እኩል ተሳታፊ፤ ሁሉም የውሳኔው ተካፋይ ሊሆን የሚችልበት የሽግግር ሂደትና መንግሥት በጋራ ሲመሰረት ብቻ እንደሆነ ጽኑ ዕምነታችን ነው። በሥልጣን ላይ ያለ ሁሉ ዘላቂ የሀገር መፍተሄ ላይ ብቸኛ ወሳኝ ፤ ሌላው ግን ከጨዋታው ውጭ አጨብጫቢና አዳማቂ መሆን አይጠበቅበትም። አማራጩ፤ መደራጀት፤ ተደራጅቶም መታጋል፤ እየታገሉ ደግሞ ለሽግግር መንግሥት ምስረታ መደላድል ሊሆን የሚችል የጋራ የተባ ተሳትፎ ብቻ ነው - በአንድ እጅ አይጨበጨብምና። ስለ ትብብር የሚነሳው እንዲያው በዘፈቀደ ሳይሆን ለሽግግር መንግሥት መሠረት የሚጥል ብቸኛው የሕዝብ የጋራ ምክር፣ ሙሉ ተሳትፎ መሆኑ አከራካሪ አይደለም።

ኢሕአፓ የዛሬ 47 ዓመት ሲመሰረት እታገልላቸዋለሁ ብሎ ካነሳቸው በርካታ ጥያቄዎች አንዱና አሁንም ድረስ መልስ ያላገኘው፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፤ የመመሥረት ጉዳይ እንደሆነ ይታወቃል። ኢሕአፓ ስለ ዴሞክራሲ ያለውን ግንዛቤ "ዴሞክራሲ ሲሉ ዴሞክራሲ ስንል" በሚል ርዕስ ፤ በልሳኑ በዴሞክራሲያ፤ በመልዕክተ ኢሕአፓ ፤ የሳተላይት ሬዲዮ ስርጭቱና በፍካሬ መፅሄት እንዲሁም በሌሎች መፅሄቶቹ በበራሪ መግለጫዎች ጭምር በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ ግልፅ በሆነ መልኩ በዝርዝር ለሕዝብ አቅርቧል።

ስለሆነም ዴሞክራሲ እንደ ፖለቲካ አስተሳሰብና አሰራር፤ እንደ መንግሥት ቅርፅና የአስተዳደር ዘይቤ ለግልም ሆነ ለጋራ እኩልነት ፤ ነፃነት፤ በደስታ መኖር ያለምንም ተፅዕኖ መናገር፤ መፃፍ ፤ መደራጀት ከቦታ ቦታ መዘዋወር፤ መብት መከበር፤ የሕግ የበላይነት መረጋገጥ ፤ ማንም ዜጋ በሕግ ፊት እኩል መሆን፤ የሕዝብ ልዕልና መከበር የሀገር የጋራ ባለቤትነት መብት መኖር፤ ...ወዘተ የሚሉት መሠረታዊ የዴሞክራሲ አስተሳሰቦችን ይዘት ያገናዘበ ሊሆን ይገባል። የነኝህን መሠረታዊ ዕምነቶች አገናዝበን ከወሰድን በዕርግጥም፤ በሀገራችን ያለፈው ግማሽ ምዕተ ዐመት፤ በተለይም የወያኔ 28 ቱን የአገዛዝ ዘመን ስናጤን፤ ዴሞክራሲ በሀገራችን እንዲመሰረት ገና እልህ አስጨራጭ ትግል የሚያስፈልግ መሆኑን ያመለክተናል። አዲሶቹ ሹመኞች ለዴሞክራሲ ከፍተኛ ቀረቤታ አለን በማለት መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ላይ ስለሚገኙ ቀረብ ብሎ መመርመሩ ፍፁም አግባብነት አለው።

ይህንን ሁኔታ አስመልክቶ፤ በዴሞክራሲያ ቅፅ 41 ቁ 5 የካቲት 2008 ዓም ይፋ በሆነው ዕትም እንደሚከተለው ተገልፆ ነበር ። እንጠቅሳለን ።

> " የኢትዮጵያ ሕዝብ በረዥም ዘመን ታሪኩ፤ ዴሞክራሲያዊ መብትን አይቶም፤ አሽትቶም ቀስሞም፤ አጣጥሞም ስለማያውቅ፤ የዴሞክራሲ ጥያቄ ዓይነተኛና ግምባር -ቀደም ጥያቄ ነበር። በየካቲት 66 ዐብዮት ማግስት ጭላንጭሉን ለማየት ዕድል አግኝቶ ነበር ለማለት ቢቻልም፤ ወዲያው ከመቅጽፈት ተዳፈነበት። ጥያቄውን አጠንክሮ ቢቀጥልም፤ ምላሽ ሳያገኝ እስከዛሬ ድረስ ልሳኑ እንደተዘጋ ቆይቷል። ጠብ-መንጃ ባነገቱ ተፈራራቂ ገዥዎች ዕብሪተኛነትና ጭካኔ ምክንያት፤ አቅም ባለማግኘቱ፤ አንገቱን ደፍቶ፤ ሞራሉን ሰብሮ ያለውድ በግድ፤ የአምባገነኖች ተገዥ ሆኖ ቀርቷል። ሀሳቡን በነፃ የመግለፅ ፤ የመጻፍ፤ የመሰብሰብ፤ ሠላማዊ ሠልፍ የማድረግ፤ መብቱ ተጨፍልቋል። የዕምነትና የኅሊና ነፃነቱ ከተገፈፈ ሰብዓዊ ፍጡር ነኝ ብሎ ራሱን ሊያታልል አይችልም። አሳዛኝና አስገራሚ የሚሆነው ነገር ደግሞ፤ ገዥዎቹ ዴሞክራሲ አምጥተንልሀልና እኛን አምነህ ተቀበል። አሜን ብለህ ተገዛ፤ ተነዳ ለማለት መሞከራቸው ነው። ገዥዎች ራሳቸውን ለመደለል ይችሉ ይሆናል። የሕዝቡን የማሰብ ችሎታና ስብዕና ዝቅ አድርጎ መገመት ግን የድንቁርና ድንቁርና መሆኑን ለመገንዘብ ከመመስከርም አልፎ በምጸት ደረጃ ያስቃል። ሕዝቡ እያረረም ቢሆን ሊስቅ ቢሞክርም፤ የዴሞክራሲ ጥያቄው እስካልተመለሰ ድረስ፤ ጥያቄውን

አንግቦ መታገሉን ይቀጥላል። የሕዝብ ጥያቄ በአመጽ መልስ ያገኛል ! የዴሞክራሲ ሥርዓት በሀገራችን በዚህም በመመርኮዝ ያነገባቸውን ዋና ዋና የትግል መፈክሮች እስካልሰፈነ ድረስ የዴሞክራሲ ጥያቄ አይዳፈንም። "

በዕርግጥ ያነገብናቸው ዋና ዋና መፈክሮችና መጠነ ሰፊ መሥዋዕት የከፈልንባቸው ጥያቄዎች እንደተገለፀውም አሁንም ህያው ናቸው። በአሁኑ ወቅትም ትግሉ፤ ምላሽን እየጠየቀ ይገኛል። ለዴሞክርሲ ሥርዓት መገንባት የሚረዱ ፤ የተለያዩና ከመንግሥት ቁጥጥር ነፃ የሆኑ የሲቪክ ድርጅቶች እንዲቋቋሙና በራሳቸው ፍላጎት ለመንቀሳቀስ ይቻላቸው ዘንድ ፤ ከምን ጊዜውም በላይ በጽናት መታገል ከሚገባው ወቅት ላይ እንገኛልን። የሲቪክና የሙያ ማኅበራት ሚና በተለይም ለዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች ሊያደርጉት የሚችሉት አስተዋፅዖ ከፍተኛ በመሆኑ፤ ነፃናታቸውን ማስጠበቅ አስፈላጊ እንደሆነ አናምናለን። ደጋግመን እንደገለፅነው፤ ኢሕአፓ ወደፊትም ቢሆን በዚህ ጎዳና ሊያበረክት የሚችለውን አስተዋጽኦ አጠንክሮ ይቀጥልበታል።

በእኛ ዕምነት ፤ ሕዝባችን መድረኩ ከተመቻቸለት፤ ከአብራኩ የሚፈልቁ ዜጎች በሚከፍሉት መሥዋዕት ነፃ ይሆናል ማለታችን ከባዶ ተስፋ ብቻ የመነጨ አይደለም ። ሕዝባችን ወደ ተሟላ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊሸጋገር ብቃቱና ብስለቱ እንዳለው በተደጋጋሚ ያስመሰከረ ለመሆኑ ቅንጣት ያህል አንጠረጠርም። ልዩ ሞግዚትም አያስፈልገውም። ሕይወት ያላቸው የሲቭክ ድርጅቶች ውጭ ዴሞክራሲን ለመገንባት የሚታሰብ አይሆንም። ማንኛውም ተንቀሳቃሽ ፖለቲካዊም ሆነ ማኅበራዊ ኃይል ሁሉ ከኢህአዴግ መዳፍ ስር ተላቅቀው በነፃ እንዲንቀሳቀሱ እስካልሆኑ ድረስ የዴሞክራሲ ጭላንጭል ተስፋ ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብም። ይልቁንስ ያልተደራጀው ተደራጅቶ፤ የተደራጀው ተጠናክሮ፤ የተጠናከረው እየተባበረ መታገል ነው አማራጩ ለጊዜው ሌላ የለም።

አሁን ያለው ሁኔታና አስተናባሪዎቹ፤ የሚቀጥለውን የምርጫ ሂደት በራሳቸው ሙሉ ቁጥጥር ስር ለማካሄድ መወሰናቸው በየጊዜው በሚዘረገፉት ፕሮፓጋንዳቸው ግልፅ አድርገዋል። ከዛሬ 44 ዓመት በፊት በወቅቱ ሥልጣን ላይ ለተቆናጠጠው የደርግ ቡድን ያቀረብነውን ጥያቄ አሁንም ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ መልኩ መልሰን ለማቅረብ የምንገደድበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ዴሞክራሲያዊ ምርጫን ለማካሄድ የሚያስችሉ፤ ሕዝባዊና ሀገራዊ ተቋማት በአግባቡ የመደራጀታቸው ጉዳይ ገና አልተነካም። ይህ በመሆኑ የሽግግር ወቅት አስፈላጊነት ከምን ጊዜውም በበለጠ ደረጃ ጎልቶ ይታያል። ከዚህም ጋር በተያያዘ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ሀገርን መጠበቅና ከጥፋት መከላከል የቅዲሚያዎች ቅድሚያ እንደሆነ ከልብ አናምናለን። ካለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመት የትግል ታሪካችን ተምረን የነበሩንን ጉድለቶች በማሟላት አስወግደን፤ በተስፋና በኅብር ትግል ተጋግዘን ሀገራችን ከተቃጣባት የጎልውና አደጋ እንታደጋት ብለን ጥሪያችንን ለሁሉም ዜጋ እናስተላልፋለን !

ተደራጅቶ እየተባበሩ በመታገል ከግባችን እንደርሳለን !

ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው !

እናቸንፋለን !